በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት

የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት

ሪፖርት

መጋቢት/ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

የዋና ዋና ግኝቶች ማውጫ/ድርሞ/ /Executive Summary/........................... 1
ክፍልአንድ…………………………………………………………………………… 3
የክትትል ኦዲቱ ዓላማ…………………………………………………………… 4
የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ……………………………………………………… 4
የክትትል ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች…………………………………………….. 5
ክፍል ሁለት………………………………………………………………………….. 6
በክትትል ኦዲቱ ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች……………………………………….. 6
የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ
የመረጃ ስርዓት የተዘረጋና የመረጃ ቋት /data base/ የተዘጋጀ ስለመሆኑ…….….…. 6
የተወረሱ ንብረቶች አመዘጋገብ እና የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና
ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ…………………………………………………….. 7
በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች መረጃ በአግባቡ መያዙን
እና በየበጀት ዓመቱ የንብረት ቆጠራ የሚደረግ ስለመሆኑ……………………………… 10
ባለስልጣኑ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ማድረጉን በተመለከተ……………..… 14
የተወረሱ መድሃኒቶች፣ምግቦችና አደገኛ እቃዎች አጠባበቅን በተመለከተ…………….. 15
በቅ/ፅ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በተቀመጠው ጊዜ
ገቢ ስለመደረጋቸውና ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ…………….. 23
የሚወረሱ ንብረቶች አጠባበቅና አወጋገድ በእስትራቴጂክና ዓመታዊ
ዕቅድ መያዙን ፣በክንውን ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሄ
እርምጃ መወሰድን በተመለከተ……………………………………………………… 24
የባለስልጣን መ/ቤቱ የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቶ ለቅ/ፅ/ቤቶች ያሰራጨ፣
ክፍተቶች በመለየት እንዲሻሻል ያደረገ መሆኑን በተመለከተ………………………….. 25
የባለስልጣን መ/ቤቱ የተሟላ የሰው ሃይል ያለው መሆኑን በተመለከተ……..………… 26
የባለስልጣን መ/ቤቱ በቅ/ፅ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት ወደ
ገቢ እንዲቀየሩ ማድረጉን በተመለከተ………………………………………………… 27
የባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ
ኮሚቴ ስለመቋቋሙና ክትትል ስለማድረጉ በተመለከተ…………………………………. 28
በአጭር ጊዜ የሚበላሹ ዕቃዎች እና አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን በአፋጣኝ
ሁኔታ እንዲወገዱና እንዲተላለፉ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ……………………….. 29
ባለስልጣን መ/ቤቱ በሽያጭ የሚተላለፉ እቃዎች ክፍያ
ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ………………………………………………………. 31
በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶችን ወደ ገቢ እንዲቀየሩ መደረጉን በተመለከተ……….……. 32
በድርድር ያልተሸጡ እቃዎች በጨረታ እንዲሸጥ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ………. 33
ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ የሚሸጣቸው እቃዎች ዝርዝርና ዋጋ
የሚያሳውቅ መሆኑን በተመለከተ………………………………………………………. 34
ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚሰራበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት

መዘርጋቱንና የመግባቢያ ሰነድ ያለው መሆኑን በተመለከተ…………………………… 34
ከአዲስ አበባ ውጪ እና አዲስ አበባ የሚገኙ ተሸከርካሪዎች ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ…………………………..……….. 35
ክፍል ሶስት………………………………………………………………………… 38
የመደምደሚያ ሀሳብ /Conclusion/………………………………………………….. 38
እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻልየታየባቸው…………………………………………….. 38
እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻልያልታየባቸው…………………………………… 39
ክፍል አራት……………………………………………………………………..……... 42
የማሻሻ ያሀሳቦች/ Recommendation/………………………………………………... 42
አባሪ 1…………………………………………………………………………………… 43
አባሪ 2…………………………………………………………………………………… 46

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)

(Executive summary)

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2006/2007 ዓ.ም በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ፤ እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው ፡-

- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ያላከ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝና ለማስወገድ ዘመናዊ የሆነ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን ያላደረገና የመረጃ ቋት/database/ ያላደራጀ በመሆኑ የተወረሱ ንብረቶች መረጃ በተደራጀ መልኩ ያልተያዘ መሆኑ፣
- በባለስልጣኑ የተዘጋጀው የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ እንዲሆን ባለመደረጉ እና ለባለሙያዎች በወቅቱ የአቅም ግንባታ እንዲያገኙ ባለማደረጉ ለተወረሱ ንብረቶች የተጋነነ ዋጋ እንዲተመን ፣ በቅ/ጽ/ቤቶች መካከል አንድ ዓይነት መስፈርት ለሌላቸው ዕቃዎች የተለያየ ዋጋ እንዲተመን እና የተወረሱ ንብረቶች በወቅቱ እንዳይወገዱ ማድረጉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለመድህኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ንብረቶች ትኩረት በመስጠት እንደ ንብረቶቹ ዓይነትና ባህሪ እስከሚወገዱ ድረስ ሊቆዩ የሚችሉበት የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን እንዲኖር እንዲሁም ንብረቶች ይዞታቸውና መሰረታዊ ባህሪያቸውን ሳይለውጡ ለደህንነታቸው

ተስማሚ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ ስለመሆናቸው በቂ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ፣

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በተመለከተ
  በስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲካተት ያላደረገ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ ለተወረሱ ንብረቶች የአያያዝ/አጠባበቅ መመሪያ ያላወጣ ሲሆን በታክስ ዕዳ ለተወረሱ ንብረቶች ያወጣው የአፈጻጸም መመሪያ አፈጻጸም ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት በወቅቱ እንዲሻሻሉ ያላደረገና ተግባራዊ ስለመደረጉ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- በባለስልጣን መ/ቤቱና በቅ/ጽ/ቤቶች በጉሙሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝ ለመጠበቅና ለማስወገድ መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሀይል የሌለው መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ያቋቋመ ቢሆንም አስወጋጅ ኮሚቴው የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ስለመወጣቱ ወቅታዊ የሆነ ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- ባስልጣን መ/ቤቱ ቶሎ የሚበላሹ አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን በሰውና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ወዲያውኑ እንዲወገዱ የማያደርግና እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ ሊያወድም የማይችላቸውን ንብረቶች ማውደም ለሚችሉ መ/ቤቶች እንዲተላለፉ አስፈሊጊውን ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በወቅቱ ለማስወገድ ከተወሰኑ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ የሌለው መሆኑ፣
- ባለስልጣኑ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ ተሸጠው ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ዋጋቸውን ለማስገመት ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፣
  እስካሁን መኖሩ ታውቋል፡፡

ክፍል አንድ

1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን፣ ገቢውን የሚሰበስበው ከሀገር ከሚገቡ፣ ከሃገር ከሚወጡ ዕቃዎች ሊይ ከሚጣል ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ከተለያዩ የታክስ ዓይነቶች ነው፡፡
2. መ/ቤቱ ከ1966 አብዮት በኋላ በነሐሴ 1967 ዓ.ም. የጉምሩክ ቀረጥና ኤክሳይዝ ታክስ አስተደደር በመባል በአዲስ መልክ ተዋቀረ፡፡ የአለም ጉምሩኮች ሕብረት ምክር ቤት ያዘጋጀውን የንግድ ሸቀጦችን በተሰሩበት ንጥረ ነገር እና በአገልግሎታቸው የሚመደበውን የታሪፍ መጽሐፍ ከነሐሴ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ፡፡
3. በ1989 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 60/1989 የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በመባል እንደገና የተቋቋመ ሲሆን፣ ተጠሪነቱም ለገቢዎች ቦርድ እንዲሆን ተደነገገ፡፡ ከዚያም በአዋጅ ቁጥር 368/1995 የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ የገቢዎች ሚንስቴር ሆነ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን" ተብሎ እንዲቋቋምና የባለስልጣን መ/ቤቱም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡
4. ከህጋዊ ነጋዴ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ በአራቱም አቅጣጫዎች የወጪ እና የገቢ ንግድ ህግን በመጣስ ዕቃዎችና ሸቀጦች ወደ ሀገር ይገባሉ ከሃገርም ይወጣሉ፡፡
5. በመሆኑም በንግድ ሥራ ክፍልና ንግድን ሊያስፋፋ በሚችል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ አደጋዎችን ይጋርጣል፡፡ በሀገር ውስጥ በኮንትሮባንድ የሚገባውን ዓይነት ተመሣሣይ፡ ምርት የሚያመርቱ ፋብሪካዎች፣ የፋብሪካ ባለቤቶችን እና ነጋዴዎችን ከገበያ ያስወጣል፡፡ ሕጋዊ አምራቾችና ነጋዴዎች ሲከስሩ ሠራተኞች ከሥራ ስሚፈናቀሉ በሀገሪቱ ላይ ሥራ አጥነት ይስፋፋል፡፡

6. የአገር ውስጥ ፋብሪካዎችና ማምረቻዎች ጥሬ ዕቃና በምርት ግብዓትነት የሚያገለግሉትን መሣሪያዎች ለመግዛት አቅም ያጣሉ፡፡ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ኢንቨስትመንት ይዳከማል፡፡መንግሥት ከገቢና ወጪ ንግድ ማግኘት የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በማሳጣት በሀገሪቱ በማስፋፋት የሚታቀደው የልማት ውጥን በአጭሩ ያስቀራል፡፡ እንዲሁም ጊዜ ባለፈባቸውና በተከለከለ የመዋቢያና የመድኃኒት ምርቶች እንዲሁም የኬሚካል ውጤት የሕብረተሰቡ ጤና ይጓደላል፡፡

7. በመሆኑም በባለስልጣን መ/ቤቱ በቅ/ጽቤቶች በጉምሩክ መቆጣጠሪያ በኮንትሮባንድ በህገወጥ መንገድ ወደ ሀገር የሚገቡና የሚወጡ እንዲሁም በታክስ ዕዳ የሚወረሱ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ መጠን ያላቸው የተለያዩ ንብረቶች በባለስልጣኑ በየጊዜው የሚወረሱ ቢሆንም እነዚህ ንብረቶች ተገቢ የሆነ የንብረት አያያዝ/አመዘጋገብ፣ አጠባበቅ በማድረግ ንብረቶቹ ሳይበላሹና መሰረታዊ ይዞታቸውን ሳይለቁ የማስወገዱ ስራ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መስራት ላይ ችግሮች የሚስተዋሉ በመሆኑ ለእነዚህ ችግሮች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

8. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2006/2007 ዓ.ም በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የላከ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

9. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው በ2008 ዓ.ም ያለውን በጀት ዓመት እና የ2009 ዓ.ም የግማሽ በጀት ዓመት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በኢትዮጵያ

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ አጠባበቅ እና አወጋገድ ላይ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መተግበራቸውን እና ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተከናወኑ ስራዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

10. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ዋና መ/ቤት እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመረጠው ከታዩ ሰባት ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች (ድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት፣ ጅግጅጋ ቅ/ፅ/ቤት ፣ አዳማ ቅ/ፅ/ቤት፣ አዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ ሚሌ ቅ/ፅ/ቤት፣ አዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና አዲስ አበባ ቦሌ ቅ/ፅ/ቤት) መካከል በአምስቱ ቅ/ፅ/ቤቶች (አዳማ ቅ/ፅ/ቤት፣ አዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ ሚሌ ቅ/ፅ/ቤት፣ አዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና አዲስ አበባ ቦሌ ቅ/ፅ/ቤት) በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክክትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

11. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች

የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት የተዘረጋና የመረጃ ቋት/data base/ የተዘጋጀ ስለመሆኑ

12. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

13. የባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ያልዘረጋና የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችል ፕሮግራሞች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያላደረገ ሲሆን እንዱሁም የንብረቶቹን ሙሉ መረጃ ማለትም መቼ እንደተወረሱ፣ መቼ እንደተወገዱና ያልተወገዱ ንብረቶችን የሚገልጽ የመረጃ ቋት/ data base/ እንደሌለው ተገኝቶ ነበር፡፡

14. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው አዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ሚሌ፣ አዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ ድሬዳዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶችን ብረቶች ተወርሰው ወደ መጋዘን ሲገቡና እና በተለያየ መንገድ ሲወገዱ መረጃቸው በዘመናዊ መልኩ ተደራጅቶ የተያዘ አለመሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

15. የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የሚወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የሆነ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት በመዘርጋት ስራ ላይ እንዲውል ሊያደርግ እና ስለ እያንዳንዱ የተወረሰ ንብረት የሚገልጽ ሙሉ መረጃ የያዘ የመረጃ ቋት እንዲደራጅ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

16. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

17. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

18. በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በጉምሩክና በታክስ ዕዲ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖልጂ ሥርዓት ያልተዘረጋ ፣ የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችለ ፕሮግራሞችና ሶፍትዌሮች

በማበልጸግ ሥራ ላይ ያልዋሉ እና የመረጃ ቋት (data base) የሌለ መሆኑን ፣ እየሠሩ ያሉት በማንዋል መሆኑን ፣

19. በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖልጂ ሥርዓት ያልተዘረጋ፣ የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችለ ፕሮግራሞችና ሶፍትዌሮች በማበልጸግ ሥራ ላይ ያልዋሉ እና የመረጃ ቋት (data base) የሌለ መሆኑን ፣ ይህ ባለመሆኑም ጨረታ ላይ ዋጋ ለመተመን፣ ቀረጥ እና ታክስ ለመተመን እየተቸገሩ መሆኑን፣

20. በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖልጂ ሥርዓት ያልተዘረጋ፣ የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችለ ፕሮግራሞችና ሶፍትዌሮች በማበልጸግ ሥራ ላይ ያልዋሉ እና የመረጃ ቋት (data base) የሌለ መሆኑን፣ ይህ ባለመሆኑ የዋጋ አተማመን ስርዓት ላይ ችግር መፍጠሩን፣ ESVS እና ASEGUDA የሌላቸው መሆኑን፣ ይህም ስራቸውን በወቅቱ እና በጊዜ እንዳይሰሩ እንቅፋት የሆነባቸው መሆኑን፣ ዋጋ ለመተመንም አዋሽ ወይም ሰመራ መሄድ እንደሚኖርባቸው፣

21. በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት የአሰራር ሥርዓቱን ለመደገፍ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችና ሶፍትዌሮች በማበልጸግ ሥራ ላይ እንዲውሉ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች ሥልጠና በመሰጠት ላይ እንደሆነ እና ወደ ሥራ ያልተገባ መሆኑን፣

22. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና የሚያግዝ Government Customs Ware house Control /GCWCS/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ከሐምሌ 1 2008 ዓ.ም ጀምሮ በሙከራ ላይ ያለ መሆኑን እና ለአምስቱም መጋዘኖች የዳታ ኢንኮደር ሰራተኛ መመደቡን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የተወረሱ ንብረቶች አመዘጋገብና እና የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

23. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

24. በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች መጋዘን ሲገቡና በተለያየ መንገድ ሲወገዱ የንብረት አመዘጋገብ ስርዓት ያለ ቢሆንም በአሰራር ስርአቱ መሰረት ተግባራዊ የማይደረግ በመሆኑ በቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ የሆነ የንብረት አመዘጋገብ የሌለ መሆኑን፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ድሬዳዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች ምን ያህል ንብረቶች እንደገቡና እንደወጡ የሚመዘገቡበት የንብረት መቆጣጠሪያ ካርድ እንደሌላቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

25. በናሙና ከታዩት በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ተሽከርካሪ በሚያዝበት ጊዜ በማቆያ ሞዳል 270 ተመዝግቦ በሞዳል 265 ውርስ ሆኖ ገቢ ሳይደረግ በቀጥታ በሞዳል 266 ወጪ የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪም ተሽከርካሪዎች ሲወረሱ ያላቸው እና የጎደላቸውን ዕቃ መረጃ የሚሞላበት የመረካከቢያ ሰነድ ያለ ቢሆንም በአቃቂ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ሚሌ፣ ድሬዳዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች በመረካከቢያ ሰነድ መሰረት የተሽከርካሪ ርክክብ የማይፈጸም መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

26. የሂሳብ አያያዝን በተመለከተ በቅ/ጽ/ቤቶችና በዋናው መ/ቤት ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገዱ ሂሳባቸው በ general ledger እንዲሁም በተላለፈላቸው ድርጅቶች ስም እንደ ጅንአድና አዲስ ፋና እና ሌሎች መ/ቤቶች ስም ተቀጽላ ሌጀር /subsidary ledger/ /የሂሳብ ቋት/ ተከፍቶ እንደማይመዘገብ እና ቅ/ጽ/ቤቶች ለጅንአድና አዲስ ፋና በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በዱቤ ሽያጭ ሲያስተላልፉ ለዋናው መ/ቤት ሂሳቡን የሚያሳውቁ ቢሆንም ዋናው መ/ቤት ግን ሂሳቡ ገቢ ሲደረግ ለቅ/ጽ/ቤቶች እንዲያውቁ እንደማያደርግ ተገኝቶ ነበር፡፡

27. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተወረሱ ንብረቶች ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የንብረት አመዘጋገብና ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ እና ተግባራዊ ሊያረጋግጥ እንዲሁም በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገድ ሂሳባቸውን ለመከታተል የሚያስችል General ledger እና subsidary ledger /ተቀጽላ የሂሳብ ቋት ሊከፍት እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

28. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

29. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

30. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መካከል በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ እና በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በጉምሩክ እዳ የተወረሱ በእቃዎቹ ላይ የንብረት መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያልተቀመጠባቸው እና እቃዎቹ ተወርሰው ገቢ የሆኑበት ዓመት የማይታወቅ ሲሆን በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ በሞዴል 265 የሚመዘገብ መሆኑን፣ በተለያየ ስሌት ሲወገዱ ደግሞ በሞዴል ቁጥር 266 ወጪ እንደሚደረግ ፣

31. በተለይ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የሚገኙ የውርስ እቃ የመጋዝን የእቃዎች ቢን ካረድ እና ስቶክ ካረድ በትክክል አለመዳረጀት እና በስነ ስርአት አለመጠቀም፣ በሞዴል /265 በሞ/266 በሞዴል /270 ገቢና ወጭ ሲደረግ የቁጥጥር ስርአት በጣም ደካማ መሆኑ፣ እቃዎች ሲገቡ የ ስሪት አገር ማርክ በትክክል አለመፃፍ እና አለመመዝገብ፣ አንድ የመጋዝን ሰራተኛ በርክክብ ጊዜ ሲያስረክብ እና ሲረከብ በልዩነት ርክክብ እንዲያደርግ ማድረግ፣ በርክክብ ጊዜ የውስጥ ኦዲተር አለመኖረ፣ የውርስ እቃ መጋዝን ገቢ ሲደረግ ትክክለኛ የሆነ መለኪያ /size/ ወይም /standared/ አለመኖር፣ በየቀኑ ገቢ የሚደረጉ እቃዎች ከፍተኛ ቦታ የሚመጡ እቃዎች በትክክል አለመመዝገቡ እና መቼ እና ማን ገቢ እንዳደረጉ የቁጥጥር ስርአት ክፍተት መኖር፣ ተሰባሪ የሆኑት እቃዎች በአንድ ላይ በጥንቃቄ ባለመቀመጣቸው የተሰበሩ እቃዎች እና የተበላሹ መኖራቸው፣ ሁሉም አይነት እቃዎች ተደራርበው እና ተደባልቀው ከመቀመጣቸው የተነሳ በቆጠራ ጊዜ እንዳይገኙ ማድረጉን ከኦዲት ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ደግሞ በሁለቱም በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ተሽከርካሪዎች በሚያዙበት ጊዜ በማቆያ ሞዴል 270 ያልተመዘገቡ መሆናቸውን እና በሞዴል 265 ውርስ ሆነው ገቢ አለመደረጋቸውን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች እና ከኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

33. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ እና ሲወጡ በገቢ እና በወጪ ደረሰኝ የሚመዘገቡ ሲሆን አመዘጋገቡም ንብረቱ እንደተያዘ በመጀመሪያ በማቆያ ሞዴል 70 ተመዝግቦ የማቆያው ሂደት ሲያልቅ ወደ ገቢ ሞዴል 265 እንደሚመዘገብ፣ በተለያየ የማስወገጃ ስልቶች ሲወገዱ በወጪ ሞዴል 266 የሚመዘገብ መሆኑን ፣ ከወጪ ቀሪውን በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችል

አመዘጋገብ እንዳላቸውና እንዲሁም በኮምፒውተር ተመዝግቦ የሚያዝ እንደሆነ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

34. ተሽከርካሪን በተመለከተ ተሽከርካሪዎች በሚያዙበት ጊዜ በማቆያ ሞዴል 270 ስለመመዝገባቸው እና በሞዴል 265 ውርስ ሆነው ገቢ ስለመደረጋቸው ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

35. የሂሳብ አያያዝን በተመለከተ በክትትሉ ኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶችና በዋናው መ/ቤት ለጅንአድና አዲስ ፋና ይሰጥ የነበረው በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የዱቤ ሽያጭ የቀረ መሆኑን እና ለማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የእጅ በእጅ ሽያጭ እንደሚከናወን ለመረዳት ተችሏል፡፡

36. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ተቆጣጣሪ መ/ቤቱ በአዳማና በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት ጉብኝቱን ባደረገበት ወቅት የተባሉት ችግሮች የነበሩ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት በተባሉትም ሆነ በሌሎች ቅ/ፅ/ቤቶች የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በሞዴል 270 ገቢ ሳይደረጉ የሚቆዩበት ችግር እንደተቀረፈ ገልፀዋል፡፡

37. ይሁን እንጂ የክትትል ኦዲት ቡድኑ በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት እና በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ተሽከርካሪዎች በሚያዙበት ጊዜ በማቆያ ሞዴል 270 ያልተመዘገቡ መሆናቸውን እና በሞዴል 265 ውርስ አለመደረጋቸውን ለመመልከት ችሏል፡፡ በመሆኑም የባለስልጣኑን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች መረጃ በአግባቡ መያዙን እና በየበጀት አመቱ ቆጠራ የሚደረግ ስለመሆኑ

38. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

39. በባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ የሚሸጡ፣ ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡና በማውደም የሚወገዱ የተወረሱ ንብረቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መረጃቸው በተሟላ እና በአግባቡ መያዛቸውን በተመለከተ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንደማይደረግ፣

40. በባለስልጣን መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በርካታ ንብረቶች ሳይወገዱ ከአምስት እስከ አስር ዓመት ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን የንብረቶች የተጠናቀረ መረጃ የሌለ መሆኑ እንዲሁም መቼ እንደተወረሱ እና የንበረቶቹ ዋጋ በገንዘብ ምን ያህል

እንደሆነ የሚያመለክት መረጃ እንደሌላቸው፣ በህግ ተይዘው ቶሎ ውሳኔ የማያገኙና ዋጋ የማይገኝላቸው ዕቃዎች መኖራቸው የሚታወቅ ቢሆንም ከእነዚህ ውስጥ ምን ያህሉ እቃዎች እንዳልተወገዱና ምን ያህል መጠን እንዳላቸው የሚገልጽ የተጠናከረ መረጃ እንዳልተዘጋጀ፣

41. እንዲሁም ስለተሽከርካሪዎች የሚገልጽ መረጃ ማለትም መቼ እንደተወረሱና ሲያዙ የነበራቸው እቃዎችን የሚያሳይ መረጃ ተጠናክሮ እንደማይያዝ፣ በጅጅጋ 38 ፣ በአዲስ አበባ ቃሊቲ 7፣ በአዳማ 3 በሚሌ 18 እና በድሬዳዋ የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ የሚገልጽ ማለትም ታርጋ ቁጥር፣ የምርት ዘመን፣ ሞዴል፣ ሻንሲ ፣ ሞተርና ሞዴል ቁጥር እና የተወረሰበት ቀን በአግባቡ ያልተመዘገበ ሲሆን እንዲሁም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተሽከርካሪዎች በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች ሳይወገዱ ጥሩ ባልሆነ ሁኔታ ተቀምጠው እንደሚገኙ፣

42. የባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳና በጉምሩክ የተወረሱ ምን ያህል ንብረቶች እንዳሉ ለማወቅና ለመከታተል ከተለያየ የስራ ሂደት ባለሙያዎች መርጦ በማዋቀር በየበጀት አመቱ ወጥ በሆነ መልኩ የንብረት ቆጠራ የማያደርግ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ በናሙና ካያቸው ከ 2003-2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የአዲስ አበባ ኤርፖርት በ2003 ፣ አቃቂ ቃሊቲ በ2004 እና አዳማ ቅ/ጽ/ቤት በ2005 ዓ.ም አንዳንድ ጊዜ ብቻ ቆጠራ ያደረጉ ሲሆን ሚሌ ፣ ድሬዲዋ እና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች የንብረት ቆጠራ አድርገው እንደማያወቁ ተገኝቶ ነበር፡፡

43. የተወረሱ ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገድ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውን ከፍ ለማድረግ፣ ለቁጥጥርና ለክትትል አመቺ ይሆን ዘንድ ንብረቶችን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው ተገቢው መረጃ በተሟላ መልኩ መያዙን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እና እንዲሁም ንብረቶቹ ለብክነትና ለምዝበራ እንዳይጋለጡ በየበጀት አመቱ ቆጠራ መደረጉን ሊከታተልና የቆጠራ ሪፖርት እንዲቀረብ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

44. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

45. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

46. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ እና በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ

ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይቶ ተገቢው መረጃ በአግባቡ መያዙን ክትትል እንደማይደረግ፣ መጋዘኖች እቃዎችን እንደዓይነታቸው ለማስቀመጥ የሚያስችል መደርደሪያ የሌላቸው ፣ እቃዎቹ ሊበላሹ በሚችሉበት መልኩ እርስ በርስ ተደራርበው እና በየዓይነታቸው ሳይሆን አንድ ላይ ተከማችተው መቀመጣቸውን እና እቃዎቹ ተወርሰው ገቢ የሆኑበት ዓመት የማይታወቅ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች እና ከኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

47. በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ ፣ በጨረታ የሚወገዱ፣ በማውደም የሚወገዱ በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መቀመጣቸውን፣ በሽያጭ የሚወገዱትን በየወሩ ጨረታ በማውጣት እንደሚያስወግዱ በቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ የተወረሱ ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶችን በአይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መረጃቸው በአግባቡ መያዙን ቢገልፁም የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የመስክ ምልከታ የተወረሱ ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶችን በአይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መረጃቸው በአግባቡ አለመያዙን ለመመልከት ተችሏል፡፡

49. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ዕቃዎችን በዓይነት ለይቶ ለማስቀመጥ የሚያስችል በቂ የዕቃ መደርደሪያ የሌላቸው ሲሆን በቀጣይ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል የመደርደሪያ ግዢ ለማከናወን በአዳማ፣ በሚሌ፣ ጋላፊ፣ ጅጅጋ፣ ሀዋሳና ሞያሌ ቅ/ፅ/ቤቶች ከዋናው መ/ቤት የምህንድስና ባለሞያ በመውሰድ የልኬት ስራው እንዲከናወን በማድረግ የበጀት ጥያቄ አቅርበው ምላሹን እየተጠባበቁ ሲሆን በጀቱ እንደተፈቀደ መደርደሪያውን በማሰራት የተባሉትን ችግሮች እንደሚፈቱ ገልፀዋል፡፡

50. የንብረት ቆጠራን በተመለከተ በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ2007 ዓ.ም እና በ 2008 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ መደረጉን ፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በ 2007 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ ሲሆን በ 2008 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ የተደረገ መሆኑን

፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት የ2008 ዓ.ም. የንብረት ቆጠራ የተደረገ ሲሆን ፣ የ2007 ዓ.ም የተደረገው የንብረት ቆጠራ ጥራት የሌለው መሆኑን እና መረጃው ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እና ከቆጠራ ሪፖርት ማስረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ባለሙያተኞችን በማዋቀር በ 2007 ዓ.ም እና በ 2008 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ የተደረገ መሆኑን የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠየቅ ቢገልፁም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

51. በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በ2008 ዓ.ም የንበረት ቆጠራ የተደረገ ሲሆን የ2007 ዓ.ም ቆጠራ ስለመደረጉ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣

52. እንዲሁም በአዋሽ ጉ/መቅ/ጣቢያ በተደረገ ጨረታ እቃዎች በጨረታ መሸጣቸውን፣ ነገር ግን አንድ አንድ እቃዎች እቃዎች ርክክብ ሲደርጉ በመጋዘን ውስጥ ማግኘት አለመቻሉን፣ በመሆኑም አስወጋጅ ኮሚቴ እቃውን ያሸነፉት ተጫራቾች ብር ቀድሞ ገቢ ያደረጉ በመሆኑ እቃቸውን ማስረከብ የመስሪያ ቤቱ ግዴታ መሆኑ ታውቆ ያሸነፉት እቃ በመጋዝን ውስጥ ባይገኝም ተመሳሳይ እቃዎች እንዲተካላቸው በመስማማት የዋጋ ጥናት ሳምፕል በአዋሽ ከተማ በመዘዋወር መረጃ ተሰብስቦ እቃዎቹ እንዲተኩ የተደረገ ሲሆን በጨረታ ተሸጦ በርክክብ ወቃት በመጋዝን ውስጥ ያልተገኘው/የጎደለው የእቃው አይነት ፡-

ሀ. የተለያዩ ዓይነት ሞባይሎች፡-

- የሞባይል ብዛት gt-l8852 Vetnam 55 ፍሬ ሲሆን በተደረገው የአካባቢው የገበያ ጥናት የአንዱ ዋጋ 1,700 ብር ሲሆን ኮሚቴው እንዲተካላቸው የወሰናቸው ሞባይሎች ፡ Samsung gm-G360 የአንዱ ግምታዊ ዋጋ 1,400 ብር ብዛት 5፣ Samsung sm-J500 HIDS የአንዱ የአካባቢው የገበያ ግምታዊ ዋጋ 1,400 ብር ብዛት 20፣ Samsung sm-J110 HIDS የአንዱ ግምታዊ ዋጋ 1,400 ብር ብዛት 30 አጠቃላይ በርክክብ ወቅት የጎደሉት 55 ሞባይሎች ጨረታውን ላሸነፉት ግለሰቦች እዲተካላችው መደረጉን፣ በተጨማሪም

- Dorodo m8000 የስሪት አገሩ china ብዛቱ 18 ሞባይሎች ሲሆን ኮሚቴው ለመተካት የወሰነው የሞባይል አይነት ደግሞ የስሪት አገሩ ቻይና M999 ብዛት 18 ሞባይሎች እንዲተካላቸው መደረጉን፣
- ሞባይል Dorodo DX ብዛቱ 02 ሲሆን ኮሚቴው ለመተካት የወሰነው ደግሞ በD X 4 ብዛቱ 02 ሞባይሎች መሆኑን፣
- mobil phon x 2 Sam sung ብዛት 05 ኮሚቴው እንዲተካ የወሰነው ደግሞ በሞባይል ቀፎ X518 ብዛቱ 05 መሆኑ፣
- ሞባይል ፎን no model ብዛቱ 01 ኮሚቴው ለመተካት የወሰነው በተመሳሳይ ሞባይሎች ፣
- የሞባይል ቀፎ Eroga-E5130 የስሪት አገሩ china ብዛት 04 ሲሆን ኮሚቴው ለመተካት የወሰነው ደግሞ በሞባይል ቀፎ TV D800 ብዛቱ 04 ፣

ለ. ዲቪዲ

- DVD Z-044 CR X በቁጥር 74 ሲሆን ኮሚቴው በአካባቢው ገበያ ባደረገው ጥናት የአንዱ ዋጋ 900 ብር ሲሆን ከዚህ እቃ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ኮሚቴው በመጋዝን ውስጥ ያገኘው እቃ DV-480 ሲሆን የአካባቢው ገበያ የአንዱ ዋጋ 850 ብር መሆኑን፣ እና የጎደለው DVD Z-044 CR X እቃ በ DV-480 እንዲተካ መደረጉን፣

ሐ. የሴት ብትን ጨርቅ

- የሴት ብትን ጨርቅ 30 ጥቃል ባለ 30 ያርድ ብዛቱ 30 ጣቃ ሲሆን ኮሚቴው ለመተካት የወሰነው ደግሞ ሺቲ ጨርቃ በጣቃ 30 ባለ 30 ያርድ ይተካላቸው በሚል መወሰኑን፣ ከጨረታ ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በቆጠራ ወቅት የታዩ ጉድለቶች እና በትርፍ የተያዙ ንብረቶች በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

ባለስልጣኑ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

53. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

54. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ የእቃዎችን ዋጋ ለመተመን የሚጠቅምበት የዋጋ መተመኛ ሲዲ በየጊዜው ወቅታዊ መሆን ያለበት ቢሆኑም ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንዲሁም በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሲዲ ዋጋ አተማመኑ የንብረተቹን ሁኔታ ያላገናዘበ የተጋነነ ዋጋ የሚተመንበት አሰራር በመኖሩ ምክንያት እቃዎቹ ሳይወገደ ለረጅም ጊዜያት የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳል በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የተወረሱ የተለያዩ ኤልክትሮኒክሰ እቃዎች በሲዲ ዋጋ አተማመን ችግር ምክንያት ከ5 ዓመት በላይ ሊወገደ አለመቻላቸውን ተገኝቶ ነበር፡፡

55. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ ያዘጋጀውን የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው የዋጋ አተማመን እንዲኖር ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

56. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

57. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

58. በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በየቅርንጫፉ ወጥ የዋጋ አተማመን አለመኖሩንና በአሰራር ላይ ቅሬታ ማስነሳቱን ከአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

59. ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት ዋጋ እየተመኑ ያሉት በ 16ኛው ሲዲ መሆኑን፣ የዋጋ መተመኛው ወቅታዊ ባለመደረጉም ዋጋ ለመተመን እየተቸገሩ መሆኑን፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በአሁኑ ጊዜ ሲዲ የቀረ መሆኑን እና ECVS እና አሲኩዳ መስመር አለመዘርጋቱን፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት የተተዉና የተወረሱ ንብረቶች የሥራ ክፍል የዋጋ ትመና አደረጃጀት የሌለው በመሆኑ የዋጋ ትመና ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን፣ በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት የዋጋ ትመና ባለሞያ የሌለ እና የዋጋ ትመና እንደማይደረግ ታውቋል፡፡

የተወረሱ መድሀኒቶች፣ ምግቦችና አደገኛ ዕቃዎች አጠባበቅን በተመለከተ፣

60. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፣

61. ባለስልጣኑ በጉምሩክ እና በታክስ ዕዳ ለተወረሱ የተለያዩ ንብረቶች እስከሚወገዱ ድረስ እንደ እቃዎቹ ዓይነትና ባህሪይ ተለይተው መቆየት የሚችሉበት የተሟላ

መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ያላዘጋጀ፣ ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ በሚቀመጡበት ጊዜ ይዞታቸውንና መሰረታዊ ባህሪያቸውን ሳይለቁ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ እንዲቀመጡ ያላደረገ መሆኑን፣

62. በናሙና በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች መድሀኒቶች፣ አደገኛ ዕቃዎችና ምግብ ነክ ነገሮች እንደ ባህሪያቸው ከሌሎች ተለይተው የማይቀመጡ ሲሆን ተዝረክርከው ንጽህናው ባልተጠበቀና ለአይጦች እና ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የሚቀመጡ መሆኑን፣

63. በአዲስ አበባ ቃሊቲ ፣ተሽከርካሪዎች ተለይተው የተቀመጡ ቢሆንም ለረጅም ግዜ ሳይወገዱ በዝናብ፣ በፀሀይ፣ በአቧራ መሰረታዊ ባህሪያቸውንና ይዞታቸውን እየለቀቁና ሳር በቅሎባቸው የሚገኙ ሲሆን እንዲሁም በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች እና በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት የተወረሱ ተሽከርካሪዎች ይዞታቸው በፀሀይ፣ በዝናብና በአቧራ እየተበላሹ የሚገኝ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

64. ባለስልጣን መ/ቤቱ እስከሚወገዱ ድረስ ለመድሀኒቶች፣ ለምግቦች፣ ለአደገኛና ለሌሎች ንብረቶች እንደ ዕቃዎቹ ዓይነትና ባህሪያቸው ተለይተው በሰውና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ተለይተው ሊቀመጡ የሚችሉበትና የተሟላ ግብአት ያለው መጋዘን ሊያዘጋጅ እንዲሁም የተወረሱ እቃዎችን በሕግ ተይዘው ጉዳይ ካለባቸው ዕቃዎች በመለየት ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

65. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

66. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

67. በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች / ለመድሀኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች / እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ያልተዘጋጀ መሆኑን እና እቃዎች ሊበላሹ በሚችሉበት ሁኔታ የተቀመጡ መሆኑን፣ ሁለት መጋዘን ብቻ ያለ ሲሆን መጋዘኖቹ መደርደሪያ የሌላቸው መሆኑን፣

68. ሁለቱም መጋዘኖች እቃዎችን እንደዓይነታቸው ለማስቀመጥ የሚያስችል መደርደሪያ የሌላቸው ፣ እቃዎች ሊበላሹ እና ሊሰበሩ በሚችሉበት መልኩ እርስ በርስ ተደራርበው እና በየዓይነታቸው ሳይሆን አንድ ላይ ተከማችተው የተቀመጡ መሆናቸውን፣ በመጋዘኖች ሌሎች የወረቀት ቁርጥራጮች እና ከአገልግሎት ውጪ

የሆኑ እና የተሰባበሩ የተለያዩ የቢሮ ቁሳቁሶች በብዛት አንድ ላይ በተወረሱ እቃዎች መጋዘን ውስጥ ተከማችተው መቀመጣቸውን፣

69. የተወረሱ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለተሽከርካሪዎች መጠለያ የሌላቸው ሲሆን፣ በፀሀይ በአቧራ እና በዝናብ የላይኛው እና የውስጥ አካላቸው በዝገት እና በአፈር የተበላሸ፣ እንዲሁም አንዳንድ አንዳንድ የውስጥ እቃዎቻቸው የጎደሏቸው መሆናቸውን ከቃለ-መጠይቅ እና ከኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ምስል 1ና2 ፡- በአዳማ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች ፀሀይና ዝናብ ተፈራርቆባቸው ያሉበት ሁኔታ

70. በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሱ ንብረቶች / ለመድሀኒት፣ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች / እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ያልተዘጋጀ መሆኑን፣ ካለው የኮንትሮባንድ ብዛት አንፃር በቂ መጋዘን የሌለ መሆኑን እና ባለስልጣን መ/ቤቱ ንብረቶቹ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን የማይከታተል እና የማይቆጣጠር እንደሆነ፣ በየጊዜው ለሚያዙ እቃዎች በቂ መጋዘን ባለመኖሩም እቃዎች ከመጋዘን ውጪ ሲቀመጡ የሚጠፉበት ሁኔታ መኖሩን፣

71. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ምግብና መድኃኒት ነክ ነገሮች ሊቀመጡበት የሚችሉ ክፍትና ማቀዝቀዣ ያላቸው

መጋዘኖች ለማሰራት የሚሆን በቂ በጀት ሊመደብ ባለመቻሉና የበጀት ጥያቄው ካለው የመንግስት የአቅም ውስንነት ሥራዎች በቅደም ተከተል የሚሰሩ በመሆኑ የተፈጠሩ ችግሮች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

72. ሶስቱም መጋዘኖች እቃዎችን እንደዓይነታቸው ለማስቀመጥ የሚያስችል መደርደሪያ የሌላቸው እና ጠባብ ሲሆኑ እቃዎቹ እርስ በርስ ተከማችተው ጣሪያ የደረሱ መሆናቸውን፣ የተለያዩ ምግብ ነክ ፣ ኤሌክትሮኒክስ ፣ አልባሳት ፣ ጫማዎች ፣ ኮስሞቲክሶች እና ሌሎች እቃዎቹ ተጨናንቀው ሊበላሹ በሚችሉበት መልኩ ጣሪያ እስኪነኩ ድረስ እርስ በርስ ተደራርበው በየዓይነታቸው ሳይሆን አንድ ላይ ተከማችተው መቀመጣቸውን፣

ምስል 3፡- በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሱ የተለያዩ እቃዎች ተደራርበውና የመጋዘኑን ጣርያ ነክተውት

73. የተወረሱ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለተሽከርካሪዎች መጠለያ የሌላቸው ሲሆን፣ በፀሀይ እና በዝናብ የላይኛው እና የውስጥ አካላቸው የተበላሸ፣ እንዲሁም አንዳንድ አንዳንድ የውስጥ እቃዎቻቸው የጎደሏቸው መሆናቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡

74. በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች / ለመድሀኒት፣ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች / እንደ አይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን የሌለ መሆኑን፣ የተለያዩ አልባሳት፣ ጨርቃጨርቅ፣ ዘይት፣ ኤሌክትሮኒክስ ፣ ስኳር፣ ሳሙና እና የተለያዩ እቃዎች በኮንቴይነር መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ

መሆናቸው፣ አንደኛው መጋዘን ሰፊ እና አብዛኛው የተወረሱ እቃዎች የተወገዱ ቢሆንም መደርደሪያ የሌለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ምስል 4 ፡- በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት በኮንቴነር ውስጥ ምግብ ነክ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣አልባሳት እና የተለያዩ እቃዎች ተቀምጠው

75. የተወረሱ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለተሽከርካሪዎች መጠለያ የሌላቸው ሲሆን፣ በፀሀይ እና በዝናብ የላይኛው እና የውስጥ አካላቸው በዝገት እና በአፈር ከመበላሸቱም በተጨማሪ የተሽከርካሪዎች አንዳንድ የውስጥ እቃዎቻቸው የጎደሉ እና የተሰበሩ መሆኑን፣ /ለምሳሌ እንደ ቴፕ፣ ስኮርት ጎማ፣መስታወት፣ ስፖኪዮ/፣ 21 አዲስ የነበሩ ተሽከርካሪዎች የላይኛው አካላቸው በዝገት እና በአፈር ለብልሽት መዳረጋቸውን እና ተሽከርካሪዎች የቆሙበት ቦታ ላይ ሰዎች እንደሚፀዳዱበት ለመመልከት ተችሏል፡፡

ምስል 5 ና 6፡- በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት የኋላ መስታወቱ የተሰበረ ተሽከርካሪ እና ተሽከርካሪዎች ያሉበት ሁኔታ

76. በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ንብረቶች እንደአይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዘታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ አራት የዕቃ መጋዘኖች መደርደሪያ ተዘጋጅቶላቸው እንደአይነታቸውና ባህሪያቸው ተለይተው የተቀመጡ ሲሆን፣ አደገኛ ኬሚካሎች በኮንቴነር የተቀመጡ መሆኑን፣

77. ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለተሽከርካሪዎች መጠለያ የሌላቸው ሲሆን በፀሀይ፣ በዝናብ እና በአቧራ የላይኛው እና የውስጥ አካላቸው እየተጎዳ የሚገኝ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

ምስል 7 ና 8 ፡- በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ተሽከርካሪዎች አቧራ፣ ፀሀይ እና ዝናብ ተፈራርቀባቸው የላይኛው አካላቸው ያለበት ሁኔታ

78. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች /ለመድሀኒት፣ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ዕቃዎች /እንደአይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዘታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው

እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘኖቹ አለመዘጋጀታቸውንና ያሉትም ምቹ አለመሆናቸውን፣

79. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በአልባሳት እና ጨርቃጨርቅ መጋዘን ውስጥ በአግባቡ ያልተያዘ መደርደሪያ ያለው መሆኑ፣ ጣሪያው የተበሳሳ ሸራ በመሆኑ ዝናብ የሚያስገባ /የሚያፈስ/ በመሆኑ ሽታ መፍጠሩን እንዲሁም ፀሀይ የሚያስገባ መሆኑን፣ በእቃዎቹ ላይ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑን፣ የህግ ሒደት ላይ ያሉት/ በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተሰጣቸው/ እቃዎች በማቆያ ሞዴል 270 ያልተያዙ መሆኑን፣ የተለያዩ ምግብ ነክ ፣ ኤሌክትሮኒክስ ፣ አልባሳት ፣ ኮስሞቲክሶች እና ሌሎች እቃዎቹ ተዘበራርቀው እርስ በርስ ለመለየት በማያስችል መልኩ መቀመጣቸውን፣

80. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በኤሌክትሮኒክስና ስፔር ፓርት መጋዘን ውስጥ በአግባቡ ያልተያዘ መደርደሪያ ያለው መሆኑ፣ ጣሪያው የተበሳሳ ሸራ በመሆኑ ዝናብ የሚያስገባ /የሚያፈስ/መሆኑ እንዲሁም ፀሀይ የሚያስገባ መሆኑን፣ በእቃዎቹ ላይ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑን፣ የህግ ሒደት ላይ ያሉት/ በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተሰጣቸው/ እቃዎች በማቆያ ሞዴል 270 ያልተያዙ መሆኑን፣ የተለያዩ ምግብ ነክ ፣ ኤሌክትሮኒክስ ፣ አልባሳት ፣ ኮስሞቲክሶች፣ መድሃኒቶች እና ሌሎች እቃዎቹ ተዘበራርቀው እርስ በርስ ለመለየት በማያስችል መልኩ መቀመጣቸውን፣

81. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በቤትና በቢሮ እቃዎች መጋዘን ውስጥ በአግባቡ ያልተያዘ መደርደሪያ ያለው መሆኑ፣ ጣሪያው የተበሳሳ ሸራ በመሆኑ ዝናብ የሚያስገባ /የሚያፈስ/መሆኑ እንዲሁም ፀሀይ የሚያስገባ መሆኑን፣ በእቃዎቹ ላይ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑን፣ የህግ ሒደት ላይ ያሉት/ በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተሰጣቸው/ እቃዎች በማቆያ ሞዴል 270 ያልተያዙ መሆኑን፣ የተለያዩ ምግብ ነክ ፣ ኤሌክትሮኒክስ ፣ አልባሳት ፣ ኮስሞቲክሶች፣ መድሃኒቶች እና ሌሎች እቃዎቹ ተዘበራርቀው እርስ በርስ ለመለየት በማያስችል መልኩ እና ሊሰበሩ በሚችሉበት ሁኔታ እርስበርስ ተደራርበው መቀመጣቸውን፣

82. በመጋዘን ቁጥር 5 ውስጥ መጋዘኑ ሙሉ ለሙሉ ቆርቆሮ ሲሆን ጣሪያው ውሃ የሚያስገባ /የሚያፈስ/ ሲሆን ወለሉ አቧራ መሆኑን፣ እንዲሁም ፀሀይ የሚያስገባ መሆኑን፣ የህግ ሒደት ላይ ያሉት/ በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተሰጣቸው/ እቃዎች በማቆያ ሞዴል 270 ያልተያዙ መሆኑን፣ የተለያዩ ምግብ ነክ ፣ ኤሌክትሮኒክስ ፣ አልባሳት ፣ ኮስሞቲክሶች፣ መድሃኒቶች እና ሌሎች እቃዎቹ ተዘበራርቀው እርስ

በርስ ለመለየት በማያስችል መልኩ እና ሊሰበሩ በሚችሉበት ሁኔታ እርስበርስ ተደራርበው መቀመጣቸውን፣

ምስል 9፡- በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ቆርቆሮ በቆርቆሮ በሆነ፣ ጣሪያው በሚያፈስ እና ወለሉ አፈር በሆነ መጋዘን ውስጥ እቃዎች የተቀመጡበት ሁኔታ

በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በተቀመጠው ጊዜ ገቢ ስለመደረጋቸውና ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ

83. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

84. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በህገወጥ መንገድ ከሀገር ሲወጡና ሲገቡ የሚወረሱ የውጭ ሀገር ገንዘቦች በ48 ሰዓት ውስጥ ከተያዙበት ቅ/ጽ/ቤት በወቅቱ ገቢ ስለ መደረጋቸው አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ፣

85. የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሰ ስድስት ሺህ (6000) የአሜሪካን ዶላር እና 3000 የሳውዲ ሪያል ከአራት ወር በላይ ገቢ ሳይደረግ በመቅረጫ ጣቢያው የሚገኝ ሲሆን ለባለስልጣኑ በወቅቱ ገቢ አለመደረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

86. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የሚያዙ የውጭ ሀገር ገንዘቦችን ቅ/ጽ/ቤቶች ለባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያሳውቁና በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢ ስለማድረጋቸው አስፈሊጊውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

87. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

88. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

89. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የባለስልጣኑ ቅ/ፅ/ቤቶች መካከል በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ የተወረሱ የውጭ ሀገር ገንዘቦች ገጥሟቸው እንደማያውቁ ሲገልፁ የቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት የተለያዩ አገር ገንዘቦች የሚያዙ ሲሆን ወዲያውኑ በቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሚገኝ ለዚሁ ከንግድ ባንክ በተከራዩዋቸው ሳጥኖች የሚቀመጥ እና የሚመነዘር መሆኑን ቢገለፅም ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

የሚወረሱ ንብረቶች አጠባበቅና አወጋገድ በእስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ መያዙንና በክንውን ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሄ እርምጃ መውሰደን በተመለከተ

90. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

91. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶች አጠባበቅ እና አወጋገድን በእስትራቴጅክ ዕቅደ የማያካትት ፣ እስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ የማያቅድ እና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት የማያዘጋጅ ሲሆን እንዲሁም አፈጻጸም ሊይ ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሄ እርምጃ እንደማይወስድ ተገኝቶ ነበር፡፡

92. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶች አጠባበቅ እና አወጋገድን በእስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያካትት እንዲሁም ስትራቴጂክ እቅድን መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ ሊያቅድና እና ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በማዘጋጀት በአፈጻጸም ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በወቅቱ የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

93. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

94. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

95. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የባለስልጣኑ ቅ/ፅ/ቤቶች መካከል በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የሚወረሱ

ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ እስትራቴጅክ ዕቅድ የሌለ /ያልተዘጋጀ/ ሲሆን ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት የሚዘጋጅ መሆኑን እና ለችግሮች የመፍትሔ እርምጃ እንደሚወሰድ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

96. የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የሚወረሱ ንብረቶች አጠባበቅና አወጋገድ በእስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ መያዙን በተያዙና የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ላይ መካተቱን ገልፀዋል፡፡

97. ይሁን እንጂ በስትራቴጂክ እቅድ ላይ ስለመካተቱ ማስረጃው ለክትትል ኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሰራጨ፣ ክፍተቶች በመለየት እንዲሻሻል ያደረገ መሆኑን በተመለከተ

98. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

99. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመቋቋሚያ አዋጁን መሰረት በማድረግ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን አወጋገድ የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣ እና ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሰራጨ ቢሆንም በአፈፃፀም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት መመሪያው እንዲሻሻል እንዳላደረገ ተገኝቶ ነበር፡፡

100. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተወረሱ ንብረቶች አያያዝ/አጠባበቅ መመሪያ ሊያወጣና እንዲሁም በታክስ ዕዳ የተያዙ ንብረቶች ለማስወገድ የወጣውን መመሪያ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ሊያሰራጭና በወጣው መመሪያ አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት እንዲሻሻል ሊያደርግ እንዲሁም ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

101. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

102. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

103. በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 56/2003 ለሁሉም የተሰራጨ ሲሆን ከቃለ-መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት መመሪያው ላይ ክፍተት በመኖሩ መሻሻል ያለበት መሆኑን፣ የመመሪያው አንቀፅ

10 ላይ የጨረታ አወጋገድ ላይ በዝግ ጨረታ ለሚሸጡ እቃዎች የ C.I.F. ዋጋ የጨረታ መነሻ ዋጋ ሆኖ የሚያገለግለው ለሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን በእቃው ላይ ለ ሶስተኛ ጊዜ ዝግ ጨረታ የተደረገ እንደሆነ ግን የእቃው መነሻ ዋጋ የእቃው F.O.B. ይሆናል የሚለው እቃዎች ቶሎ እንዳይሸጡ ያደረገ መሆኑን፣ ሌላው መመሪያው እቃዎች በሲ.ዲ ዋጋ ይሸጥ የሚለው ሲሆን፣ በኮንትሮባንድ የተወረሱ ንብረቶች አብዛኛዎቹ መረጃ ስለማይገኝላቸው በ ሲ.ዲ ዋጋ ትመና ለመሸጥ የማይመች መሆኑን እና በኮንትሮባንድ ለተወረሱ ንብረቶች የተለየ የዋጋ መተመኛ ሊኖረው እንደሚገባ፣

104. በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት መመሪያው ወቅታዊ ባለመደረጉ የማያሰራ መሆኑ ስለታመነበት እንዲሻሻል ለውይይት ቀርቦ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለአፈጻጸም በሂደት ላይ መሆኑ፣ መመሪያው በተለያየ መንገድ የተወረሱ እቃዎች በ ሲ አይ ኤፍ (CIF) የዋጋ ትመና ወጥቶ ሦስት ጊዜ ጨረታ ከወጣ በኋላ በ ፎብ (FOB) ይሸጥ የሚል መሆኑ፣ የሲ አይ ኤፍ (CIF) የዋጋ ትመና እቃው ገበያ ላይ ካለው ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ በመሆኑ የማይሸጥ መሆኑ፣ ይህም እቃዎቹ እንዲበላሹ የሚያደርግ ሲሆን የፎብ (FOB) የዋጋ ትመናም ቢሆንም ከ (CIF) የዋጋ ትመና የኢንሹራንስና የማጓጓዣ ወጪ ብቻ ስለሚቀነስበት ብዙም ልዩነት የሌለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ የተሟላ የሰው ሃይል ያለው መሆኑን በተመለከተ

105. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

106. በለስልጣን መ/ቤቱና በቅ/ጽ /ቤቶች በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለማስወገድ የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የሰው ሀይል እንዳልተሟላላቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

107. ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለማስወገድ መዋቅሩን መሰረት በማድረግ የተሟላ የሰው ሃይል እንዲኖር ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

108. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

109. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

110. በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በጉምሩክ እና በታክስ አዲ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስተዳደርና ለማስወገድ የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሃይል የሌለ መሆኑን በመዋቅሩ መሰረት የሚያስፈልገው 13 ባለሞያ ሲሆን አሁን ያለው 8 ባለሞያ መሆኑን እና እንርሱም በሙያው የሰለጠኑ አለመሆናቸውን፣ የዋጋ ትመና ባለሞያ የሌለ መሆኑን፣

111. በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በመዋቅሩ መሰረት የተፈቀደው የሰው ሀይል ብዛት 10 ሲሆን አሁን ያለው የሰው ሀይል ደግሞ 4 መሆኑን፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት

112. በመዋቅሩ መሰረት የተፈቀደው የሰው ሀይል ብዛት 7 ሲሆን አሁን ያለው የሰው ሀይል ብዛት 5 መሆኑን እና የዋጋ ትመና ባለሞያ የሌላቸው መሆኑን፣

113. በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በመዋቅሩ መሰረት የተፈቀደው የሰው ሃይል ብዛት አስራ ስምንት (18) ሲሆን፣ አሁን አምስት መደቦች ክፍት መሆናቸውን፣

114. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ባለስልጣን መ/ቤቱ እና በቅ/ጽቤቶች በጉምሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስተዳደርና ለማስወገድ የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሃይል መኖሩን አስመልክቶ የተሟላ የሰው ኃይል አለመኖሩን በክትትል ኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት ወደ ገቢ እንዲቀየሩማድረጉን በተመለከተ

115. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

116. በተለያዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት በተያዙ በአምስት የስራ ቀን ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ተደርገው ወደ ገቢ እንዲቀየሩ መደረግ ቢኖርባቸውም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ቅ/ጽ/ቤቶችና ቃለመጠይቅ ከተደረገላቸው የስራ ኃላፊዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው በቅ/ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት በመመሪያው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደማይቀየሩ ተገኝቶ ነበር፡፡

117. ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት በቆይታ መሰረታዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ተላልፈው ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውሉ ሊያደረግና በወቅቱ ወደ ገቢ ሊቀየሩ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

118. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

119. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

120. በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በ20/12/2008 ዓ.ም ብዛታቸው 112,340 የዋጋ ግምታቸው 2,246,800 የሆነ የብር ጌጣጌጥ፣ እንዲሁም በ04/02/2009 ዓ.ም 68,745.52 ግራም የተለያዩ የብር ጌጣጌጦችና 519.92 ግራም አርቴፊሻል የአንገት ሀብል፣ እንዲሁም በቀን 02/02/09 መጠኑ 70.202 ግራም የሆነ የብር ጌጣጌጣች ተይዘው ወደ ዋናው መ/ቤት የላኩት መሆኑን እና ዋናው መ/ቤትም ወደ ገቢ የቀየራቸው መሆኑን በቃለ-መጠይቅ እና በማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

121. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቶች የተያዙ የከበሩ ማዕድናት በተመለከተ ወደ ተያዙና የተወረሱ እቃዎች ቡድናቸው የሚመጣ ነገር እንደሌለና ይህን የሚየስተናግድ በስራ አስኪያጅ የተቋቋመ ሌላ ክፍል ወይም ኮሚቴ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ስለመቋቋሙና ክትትል ስለማድረጉ በተመለከተ

122. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

123. የባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴዎች ከተለያዩ የስራ ሂደቶችና ባለድረሻ አካለት በማካተት ያቋቋመ ቢሆንም ኮሚቴው የተሰጠውን ተግባርና ሀላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ አስፈሊጊውን ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ እንዳልሆነ፣

124. በባለስልጣኑ የተቋቋመው ኮሚቴ በተለያዩ ጊዜያት የተ.ያዩ እቃዎችን ያስወገደ ቢሆንም የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በተሟላ ሁኔታ ከመወጣት አንጻር ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ ንብረቶች ላይ ትኩረትና ክትትል በማድረግ ንብረቶቹ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲተላለፉ አለማድረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

125. ባለስልጣኑ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴው የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ስለመወጣቱ የሚያከናውናቸውን ተግባራት፣ የሚያጋጥሙትን ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ በማድረግ የተወረሱ ንብረቶች በወቅቱ እንዲወገዱ ስለማድረጉ አፈጸጸሙን ሊከታተል እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

126. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

127. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

128. በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን በታክስ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን እቃዎችን የሚያስወግደው ኮሚቴው መሆኑን፣ ነገር ግን የተወረሱ ንብረቶች በፍጥነት እየተወገዱ አለመሆናቸውን፣ አስወጋጅ ኮሚቴ ቀልጣፋ ስራ እየሰራ አለመሆኑን፣

129. በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በታክስ እዳና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በተመለከተ ሁለት ዓይነት ኮሚቴዎች ማለትም የአስወጋጅ እና የጨረታ ኮሚቴ መኖሩ፣ አብዛኛው ሥራ መሰራት ያለበት በኮሚቴው መሆኑን በመመሪያ ቁጥር 56/2003 ላይ የተቀመጠ ቢሆንም በአብዛኛውን የኮሚቴው ሥራዎችን የሚያከናውነው የተተዉና የተወረሱ ንብረቶች ቡድኑ መሆኑን፣

130. በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴውም አፈፃፀሙን የሚከታተል መሆኑን ከቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጭር ጊዜ የሚበላሹ ዕቃዎች እና አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን በአፋጣኝ ሁኔታ እንዲወገዱና እንዲተላለፉ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ

131. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

132. ባለስልጣኑ በአጭር ጊዜ የሚበላሹ እና አደገኛ የሆኑ የተወረሱ ንብረቶችን በአፋጣኝ ሁኔታ እንዲወገዱ ያላደረገ እና በባለስጣኑ ሊወድሙ የማይችሉ አደገኛ ወይም የተከለከለ ዕቃዎች እንዲወድሙ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት በወቅቱ እንዲተላለፉ እንዳላደረገ ተገኝቶ ነበር ፡፡

133. ባለስልጣን መ/ቤቱ ቶሎ የሚበላሹና አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን በአከባቢና በማህበረሰቡ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉ ችግሮችን ትኩረት በመስጠት ወዲያውኑ እንዲወገድ ሊደረግና፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ሊያወድም የማይችላቸውን ለማውደም ብቁ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት ንብረቶቹ ቶሎ እንዲተላለፉ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

134. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

135. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

136. በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ኬሚካል እየተወገደ አለመሆኑን፣ ይህንን በተደጋጋሚ ለዋናው መ/ቤት በደብዳቤ ቢያሳውቁም ምላሽ ያላገኙ ሲሆን በተጨማሪም በ2003 ዓ.ም በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወር ተይዞ የተወረሰ የዝሆን ጥርስ ቢኖርም በማን እና

137. እንዴት መወገድ እንዳለበት መመሪያ የሚሰጥ አካል በመጥፋቱ እስካሁን የተቀመጠ መሆኑን፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኮንቴነር የተያዙ ያልተወገዱ ኬሚካሎች መኖራቸውን እነሱን ለማስወገድ ለዋናው መ/ቤት በተደጋጋሚ ደብዳቤ ያሳወቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

138. በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በህገወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ ሊገባ ሲል ተይዞ የነበረ በቁጥር 3,546,000 ወይም 591 ካርቶን ቢክ እስኪርቢቶ ሳይወገድ ከ 6 ዓመት በላይ በኮንቴይነር ውስጥ መቀመጡ፣ በ06/06/2008 ዓ.ም ለጨረታ ቀርቦ የቀረበው ዋጋ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ የተሰረዘ መሆኑን፣ በ 22/07/2008 ዓ.ም በድጋሚ ጨረታ ወጥቶበት የተሻለ ዋጋ የተገኘበት ቢሆንም እስኪብርቶዎች ሲሞከሩ ለብዙ ዓመታት በኮንቴይነር ውስጥ የቆዩ በመሆናቸው አብዛኛው የማይሰራ፣ የደረቀና አንዳንዱ ደግሞ የሚያቆራርጥ መሆኑን፣ በዚሁም መሠረት የእቃውን ጥራት ለማረጋገጥ ለኢትዮጵያ ተስማሚነት እና ምዘና ድርጅት በቁጥር 2.23/117/08 በቀን 22/09/2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ 100 የእስኪርቢቶ ናሙና ይዘው ያቀረቡ ሲሆን ድርጅቱም በቁጥር 2/15/6-2/900/08 በቀን 15/10/2008 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ መሰረት የጥራት ደረጃው ለፅሁፍ አገልግሎት የማይውል መሆኑን ያሳወቃቸው መሆኑን የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሚሌ ቅ/ፅ/ቤት በቁጥር 2.16/57/09፣ በቀን 01/03/2009 ዓ.ም ለተያዙና የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ቡድን በፃፈው ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ምስል 10፡-በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት በወቅቱ ባለመወገዱ ከጥቅም ውጪ የሆነ ኮንቴነር ሙሉ ቢክ እስኪርቢቶ

ምስል 11፡- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በ2003 ዓ.ም በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወር ተይዞ ያልተወገደ የዝሆን ጥርስ

139. በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ያልተወገዱ ኬሚካሎችና መድሐኒቶች መኖራቸውንና እንዲወገዱ ለምግብና መድሐኒትና ቁጥጥር ባለሥልጣን በተደጋጋሚ በደብዳቤ ቢያሳውቁም ሊወገድላቸው አለመቻሉን፣ ግቢው ውስጥ ሶስት ኮንቴነር ያልተወገደ አደገኛ ኬሚካል መቀመጡን እንዲሁም ባዶ ቦታ ላይ ያለምንም ከለላ ከአይሮፕላኑ ማቆሚያ በግምት 30 ሜትር ላይ ሳይወገዱ የተቀመጡ ተቀጣጣይ ኬሚካሎች መኖራቸውን ከቃለ-መጠይቅ እና ከኦዲት ቡድኑ የመስክ ላይ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡



ምስል 11 ፡- ከአይሮፕላን ማቆሚያው በግምት 30 ሚትር ላይ ፀሀይ ላይ በበርሜል የተቀመጠ ተቀጣጣይ ኬሚካል

ምስል 12፡- ለረጅም ጊዜ ሳይወገድ በኮንቴነር እና ከኮንቴነር ውጪ የተቀመጠ አደገኛ ኬሚካል

ባለስልጣን መ/ቤቱ በሽያጭ የሚተላለፉ ዕቃዎች ክፍያ ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

140. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

141. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ ሽያጭ ለሚተላለፉ ወይም ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በክፍያ ለሚረከቧቸው ዕቃዎች ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ ለባለስልጣኑ ገቢ ስለማድረጋቸው ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር እንደማያደርግ ተገኝቶ ነበር፡፡

142. በዱቤ ሽያጭ የሚተላለፉ የተወረሱ ንብረቶች ክፍያ የሂሳብ ቋት እንዲኖር ሊያደርግና በውሉ መሰረት ገቢ መደረጉን አስፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

143. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

144. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

145. በክትትል ኦዲቱ በናሙና በታዩ በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፣በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በሽያጭ ለሚተላለፉ ወይም ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በክፍያ ለሚረከቧቸው ዕቃዎች የክፍያ አፈጻጸሙም እጅ በእጅ ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም ከጅንአድና አዲስ ፋና ጋር የነበረው የዱቤ ሽያጭ ውል የተቋረጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

146. እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ከሁሉም ክልሎችና ከተማ በጉምሩክ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የተወረሱ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች፣የምግብ ማጣፈጫዎች እና ቅመማ ቅመሞች፣ የፅዳት እቃዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች(ደረቅ እና ፈሳሽ ሳሙና የጥፍር መቁረጫ ምላጭ የመሳሰሉት)፣ የአዋቂ የወንድና የሴት አልባሳት እና ጫማ፣ የህፃናት የወንድና የሴት አልባሳት እና ጫማ፣ የምግብ ማብሰያ እና መመገቢያ ቁሳቁሶች፣ እና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች ለኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን በስጦታ እንደሚሰጥ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በደብዳቤ ቁጥር 5.0/470/08 እና በቀን 22/11/2008 ዓ.ም ለቅ/ፅ/ቤቶች በሙሉ ከፃፈው ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶችን ወደ ገቢ እንዲቀየሩ መደረጉን በተመለከተ

147. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

148. በታክስ ዕዳ የተወረሰ ንብረት ባለንብረቱ ዕዳውን እንዲከፍሉ ከተነገረበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ ክፍያውን ካልፈጸመ ንብረቱ ተሽጦ ዕዳው መከፈል ያለበት ቢሆንም በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶች መመሪያውን መሰረት በማድረግ በወቅቱ ወደ ገቢ እንዲቀየሩ አለመደረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

149. ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ እዳ የሚወረሱ ንብረቶችን በመመሪያው መስረት በወቅቱ ወደ ገቢ በመቀየር ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን ማሳደግና የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

150. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

151. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

152. በአዳማ ገቢዎች ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶችን የማይሸጡ መሆኑን፣ የሚሸጡት በዋናው መ/ቤት በኩል መሆኑን፣ ይህም የሲጀር ስራን ደካማ ያደረገው መሆኑን ፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በታክስ እዳ የተያዙ ቃዎች ዋናው መ/ቤት የሚረከብ መሆኑ እና ቅ/መ/ቤቱ የማይመለከተው ሲሆን ፣ ነገር ግን የጉምሩክ የቀረጥ ታክስ ሳይከፍሉ የሚገቡትን ተሽከርካሪዎች የሚወርስ መሆኑን ፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት፣ በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶች አለመኖሩን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

በድርድር ያልተሸጡ እቃዎች በጨረታ እንዲሸጥ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ

153. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

154. በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአዲስ አበባ ቃሊቲ፣ በሚሌና በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች የተወረሱ ተሽከርካሪዎች ጉዳያቸው በህግ ከተያዘ በዋናነት ጅንአድ አልወስድ ያላቸው በርካታ ግምት ያላቸው እቃዎች ያለ ቢሆንም ጨረታ በማውጣት እንዲወገድ አለመደረጉ፣

155. በባለስልጣን መ/ቤቱ አዲስ አበባ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ድሬደዋ ፣ ሚሌ ፣ ጅጅጋ፣ ሞያሌ ፣ ባህርዳር ፣ ኮምቦልቻ ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዋናነት ጅንአድ እና ሌሎች መ/ቤቶች አልወስድ ያሏዋቸው ግምታቸው የማይታወቅና የተጠናቀረ መረጃ የሌላቸው ዕቃዎች ያለ ሲሆን በተለይ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ የተከማቹ ከፍተኛ ግምት ያሏቸው አሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የተለያየ ሞዴል ያሏቸው

የሞባይል ቀፎዎች እና ሌሎች ዕቃዎች በጨረታ እንዲወገዱ አለመደረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

156. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት መ/ቤቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን ዕቃዎች በመለየት ክምችት ሳይፈጥሩና ይዞታቸውን ሳይለቁ በጨረታ እንዲሸጡ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

157. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

158. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

159. በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን እቃዎች በጨረታ እንዲሸጡ የሚደረግ መሆኑን ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በዱቤ የሚሸጣቸውን እቃዎች ዝርዝርና ዋጋ የሚያሳውቅ መሆኑን በተመለከተ

160. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

161. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ አዲስ እቃዎችን በዱቤ ሽያጭ ለጅንአድና ለአዲስ ፋና የሚያስተላልፍ ሲሆን ነገር ግን በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች የዕቃዎችን ዝርዝር፣ምን ያህል ብዛት እንዳላቸው እና ዋጋቸው ምን ያህል እንደሆነ በማስላት ወጥ በሆነ መልኩ በቅድሚያ ለገዢዎች የማያሳውቅ መሆኑን ተገኝቶ ነበር፡፡

162. ባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ የሚሸጡትን የተወረሱ ዕቃዎች ክፍያቸውን በወቅቱ ለመሰብሰብ አለመግባባት እንዳይፈጠር የሚሸጥበትን ዋጋና የእቃውን ዝርዝር በመግለጽ በቅድሚያ ለገዢ ሊያሳውቅ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

163. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

164. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

165. በክትትል ኦዲቱ በናሙና በታዩ በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፣በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፣ በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት የዱቤ ሽያጭ የቀረ ሲሆን አሁን ያለው የክፍያ አፈጻጸሙም እጅ በእጅ መሆኑን እና ከዚህ ቀደም ከጅንአድና አዲስ ፋና ጋር የነበረው የዱቤ ሽያጭ ውል መቋረጡን የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የሚሰራበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና የመግባቢያ ሰነድ ያለው መሆኑን በተመለከተ

166. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

167. በባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠበቅና ለማስወገድ እንደ ንብረቶቹ አይነትና ባህሪ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ በቅንጅት የሚሰራበት ሁኔታ የላላ እና በዚህ ዙርያ ከሚመለከታቸው ከጅንአድና እና ከአዲስ ፋና በስተቀር ከጤና ጥበቃ፣ ከጤና ስነ ምግብ ክብካቤ ባለስልጣን፣ ከቅርስ ፣ከመከላከያ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ እንደሌለው ተገኝቶ ነበር፡፡

168. ባለስልጣኑ በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን እንደ ዕቃዎች አይነትና ባህሪ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

169. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

170. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

171. ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ የአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከክልሉ ገቢዎች እና ከክልሉ ፖሊስ ጋር ብቻ በቅንጅት የሚሰሩ መሆኑን፣ የአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ከፌዴራል ፖሊስ ጋር ብቻ አብረው የሚሰሩ መሆኑን፣ የሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ከፌዴራል ፖሊስ እና ከክልሉ ፖሊስ ጋር አብረው የሚሰሩ መሆኑን ፣ የቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ከምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ፣ ከጥራትና ደረጃዎች ቁጥጥር ባለስልጣን ፣ ከመንገድና ትራንስፖርት ባለስልጣን፣ ከባሕርና ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን እና ከፌዴራል ፖሊስ ጋር አብረው እንደሚሰሩ ፣የቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ከፌዴራል ፖሊስ ጋር ብቻ አብረው

እንደሚሰሩ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ ሲሆን ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ከባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ የሌላቸው መሆኑን አክለው ገልፀዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ውጪ እና አዲስ አበባ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ

172. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

173. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ ባለ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ እዲስ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ ተሸጠው ሂሳባቸው በወቅቱ ገቢ እንዲሆን ለማስቻል የመነሻ ዋጋ ለማሰራት ከመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት እና አግባብነት ካላቸው የክልል መንግስት መ/ቤቶች ጋር ቀልጣፋ እና ውጤታማ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት እንዳልዘረጋ፣

174. በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ እዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በዋጋ ግምት ምክንያት ሳይወገድ ለረጅም ግዜ የተቀመጡ ሲሆን ነገር ግን ዋጋ ለማስገመት ከመንገድ ትራንስፖርት ሚንስቴር መ/ቤት ጋር በቅንጅት ስለመስራቱ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ሊቀርብ አለመቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

175. በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ የተወረሱ በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጪ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በጨረታ/በሀራጅ ለመሸጥ የዋጋ ግምት ለማሰራት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

176. ባለስልጣን መ/ቤቱ የድርጊት መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አላከም፡፡

177. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

178. በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የመነሻ ዋጋ የሚወስዱት ከቀረጥ እና ታክስ ዋጋ ሲሆን ቀጥሎ ወደ C.I.F. የሚመጣ መሆኑን ተሽከርካሪው ካልተሸጠ ወደ መንገድ ትራንስፖርት ትመና የሚሔዱ መሆኑን፣ አምስት ጊዜ ጨረታ ወጥቶባቸው በተሽከርካሪው ላይ ያሉ የተለያዩ ለሽያጭ የሚሆኑ ማስረጃዎች ባለመኖራቸው ያልተሸጡ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን፣

179. በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በታክስ እዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ መነሻ ዋጋ የሚሆን የንብረት ዋጋ ግምት ከመንገድ ትራንስፖርት እና

አግባብነት ካላቸው የክልል መንግስታት መ/ቤቶች ጋር በትብብር የማይሰራ መሆኑን፣ ተሽከርካሪ በጣቢያቸው ተወግዶ እንደማያውቅ እና ተሽከርካሪ ለማስወገድ ባለሞያ የሌላቸው መሆኑን፣

180. በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት መንገድ ትራንስፖርት መጀመርያ ተሽከርካሪዎችን እንዲፈትሽላቸውና መረጃ ለሌላቸው የንብረት ዋጋ ግምት እንዲያወጣላቸው እንደሚያደርጉ፣ በአመቱ ውስጥ የተወገዱ ተሽከርካሪዎች በመንገድ ትራንስፖርት ትብብር እንደተወገዱ መሆኑን፣ በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት በታክስ እዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች የዋና መ/ቤቱ ኃላፊነት እንደሆነ ከሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

181. በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ተሽከርካሪ ሽጠው የማያውቁ መሆኑን፣ በ2001 ዓ.ም የተያዙ 24 የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎች ያሉ ሲሆን ተሽከርካሪዎች ከ 2001 ዓ.ም ጀምሮ በማቆያ ሳይገቡ ወይም ውርስ ሳይሆኑ የቆዩ መሆኑን፣ ከእንዚህ ተሽከርካሪዎች መካከል ከጥቅምት 13/2008 - ህዳር 12/2008 ዓ.ም. ድረስ የሚሌ ቅ/ፅ/ቤት በወጣው ማስታወቂያ መሠረት የመኪኖች ባለቤት የሆነና እስካሁን ለምን እንደተያዙና ንብረቶቻችውን ለምን መጥተው እንዳልጠየቁ መረጃ ከሰጡት መሀከል የ8 ተሽከርካሪዎች ባለቤቶች ተጠይቀው ተሽከርካሪውን የተውት ከአቅም በላይ ቀረጥ ተጠይቀው የገለፁ ሲሆን አጠቃላይ ዝርዝሩ በአባሪ 2 ቀርቧል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

182. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡ እነርሱም፡-

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት እና በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና የሚያግዝ Government Customs Ware house Control /GCWCS/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ከሐምሌ 1 2008 ዓ.ም ጀምሮ በሙከራ ላይ ያለ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ እና ሲወጡ በገቢ እና በወጪ ደረሰኝ የሚመዘገቡ ሲሆን አመዘጋገቡም ንብረቱ አንደተያዘ በመጀመሪያ በማቆያ ሞዴል 70 ተመዝግቦ የማቆያው ሂደት ሲያልቅ ወደ ገቢ ሞዴል 265 እንደሚመዘገብ፣ በተለያየ የማስወገጃ ስልቶች ሲወገዱ በወጪ

ሞዴል 266 የሚመዘገብ መሆኑን ፣ ከወጪ ቀሪውን በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችል አመዘጋገብ እንዳላቸውና እንዲሁም በኮምፒውተር ተመዝግቦ የሚያዝ እንደሆነ፣

- በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት የተወረሱ ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ ፣ በጨረታ የሚወገዱ፣ በማውደም የሚወገዱ በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መቀመጣቸው፣ በሽያጭ የሚወገዱትን በየወሩ ጨረታ በማውጣት እንደሚያስወግዱ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በዋናው መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች በጉምሩክ እና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ዓይነት፣ ብዛት እና ያለበትን ሁኔታ ለማወቅና ለመከታተል ከተለያዩ የሥራ ሂደቶች ባለሙያዎች መርጦ በማዋቀር በየበጀት አመቱ የንብረት ቆጠራ እያደረገ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን እቃዎች በመለየት መመሪያውን መሰረት በማድረግ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች (ወጥ በሆነ መልኩ) በጨረታ እንዲሸጡ መደረጉ፣
- ባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የዱቤ ሽያጭ መቅረቱ እና የእጅ በእጅ ሽያጭ መከናወኑ፣

3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ያላከ መሆኑ፣
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት ፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ እና በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝና ለማስወገድ ዘመናዊ የሆነ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን ያላደረገና የመረጃ ቋት/database/ ያላደራጀ በመሆኑ የተወረሱ ንብረቶች መረጃ በተደራጀ መልኩ ያልተያዘ መሆኑ፣ እንዲሁም በቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት እና በቦሌ ቅ/ፅ/ቤት እና በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና የሚያግዝ Government Customs Ware house Control /GCWCS/ የተባለ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ወደ ስራ ያልተገባበት ሲሆን ቀሪ የሚስተካከሉ ነገሮች ያሉት መሆኑ፣
- በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ እና በሚሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በጉምሩክ እዳ የተወረሱ እቃዎቹ ላይ የንብረት መቆጣጠሪያ ቢን

ካርድ ያልተቀመጠባቸው እና እቃዎቹ ተወርሰው ገቢ የሆኑበት ዓመት የማይታወቅ መሆኑ፣

- ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ በአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ተሽከርካሪዎች በሚያዙበት ጊዜ በማቆያ ሞዴል 270 ያልተመዘገቡ መሆናቸውን እና በሞዴል 265 ውርስ ሆነው ገቢ አለመደረጋቸው ፣
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት፣ በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ እና በሚሌ ቅ/ፅ/ቤት በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይቶ ተገቢው መረጃ በአግባቡ መያዙን ክትትል እንደማይደረግ፣ መጋዘኖች እቃዎችን እንደዓይነታቸው ለማስቀመጥ የሚያስችል መደርደሪያ የሌላቸው ፣ እቃዎቹ ሊበላሹ በሚችሉበት መልኩ እርስ በርስ ተደራርበው እና በየዓይነታቸው ሳይሆን አንድ ላይ ተከማችተው መቀመጣቸውን እና እቃዎቹ ተወርሰው ገቢ የሆኑበት ዓመት የማይታወቅ መሆኑ፣
    - በባለስልጣኑ የተዘጋጀው የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ እንዲሆን ባለመደረጉ እና ለባለሙያዎች በወቅቱ የአቅም ግንባታ እንዲያገኙ ባለማደረጉ ለተወረሱ ንብረቶች የተጋነነ ዋጋ እንዲተመን ፣ በቅ/ጽ/ቤቶች መካከል አንድ ዓይነት መስፈርት ለሌላቸው ዕቃዎች የተለያየ ዋጋ እንዲተመን እና የተወረሱ ንብረቶች በወቅቱ እንዳይወገዱ ማድረጉ፣
    - ባለስልጣን መ/ቤቱ ለመድሀኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች ንብረቶች ትኩረት በመስጠት እንደ ንብረቶቹ ዓይነትና ባህሪ እስከሚወገዱ ድረስ ሊቆዩ የሚችሉበት የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን እንዲኖር እንዲሁም ንብረቶች ይዞታቸውና መሰረታዊ ባህሪያቸውን ሳይለውጡ ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነ ሆኔታ የተቀመጡ ስለመሆናቸው በቂ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ፣
    - ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በተመለከተ በስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲካተት ያላደረገ መሆኑ፣
    - ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ ለተወረሱ ንብረቶች የአያያዝ/አጠባበቅ መመሪያ ያላወጣ ሲሆን በታክስ ዕዳ ለተወረሱ ንብረቶች ያወጣው የአፈጻጸም መመሪያ

አፈጻጸም ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት በወቅቱ እንዲሻሻሉ ያላደረገና ተግባራዊ ስለመደረጉ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ የማያረጋግጥ መሆኑ፣

- በባለስልጣን መ/ቤቱና በቅ/ጽ/ቤቶች በጉሙሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመያዝ ለመጠበቅና ለማስወገድ መዋቅሩን መሰረት ያደረገ የተሟላ የሰው ሀይል የሌለው መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ያቋቋመ ቢሆንም አስወጋጅ ኮሚቴው የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ስለመወጣቱ ወቅታዊ የሆነ ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣
- ባስልጣን መ/ቤቱ ቶሎ የሚበላሹ አደገኛ የሆኑ ንብረቶችን በሰውና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ወዲያውኑ እንዲወገዱ የማያደርግና እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ ሊያወድም የማይችላቸውን ንብረቶች ማውደም ለሚችሉ መ/ቤቶች እንዲተላለፉ አስፈሊጊውን ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን በወቅቱ ለማስወገድ ከተወሰኑ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ የሌለው መሆኑ፣
- ባለስልጣኑ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ዕዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ ተሸጠው ወደ ገቢ እንዲቀየሩ ዋጋቸውን ለማስገመት ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፣

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

183. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

184. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የድርጊት መርሃ ግብርም ተዘጋጅቶ ለመ/ቤታችን መላክ አለበት፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት እና ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ በንብረት ቆጠራ ወቅት የጎደሉ እና ትርፍ ሆነው የተገኙ የተለያዩ እቃዎች

ሀ/ በጉድለት የተገኙ

ተ.ቁ	የእቃው አይነት	መ.ቁ/ ማርክ	የስሪት ሀገር	መለኪያ	ከወጭ ቀሪ	በቆጠራ የተገኘ	በጉድለት የተገኘ
1	የህፃናት መታቀፊያ	-	-	በቁጥር	245	244	-1
2	የሴቶች ነጠላ ጫማ	-	ቻይና	በቁጥር	1628	1625	-3
3	የልጆች ቱታ ሱሪ	-	-	በቁጥር	195	194	-1
4	የሴት ልጆች ነጠላ ጫማ	-	-	በቁጥር	272	268	-4
5	TV-LED 50 inchi	LG	-	በቁጥር	7	6	-1
6	Reciver	Super max-9200	china	በቁጥር	2	0	-2
7	የአዋቂ ብርድ ልብስ		ቻይና	በቁጥር	16	15	-1
8	ሺቲ ጣቃ	-	-	በቁጥር	2	0	-2
9	የልጆች ሸሚዝና ቁምጣ	-	-	በቁጥር	14	11	-3
10	Rod sub assy	13201-29716	japan	በቁጥር	2	0	-2
11	Bearing	የእቃው serial number የጠፋ	japan	packet	7	3	-4
12	Gasket cylinder	-	japan	በቁጥር	1	0	-1

ለ/ በትርፍ የተገኙ

ተ.ቁ	የእቃው አይነት	መ.ቁ/ ማርክ	የስሪት ሀገር	መለኪያ	ከወጭ ቀሪ 8=4-7	በቆጠራ የተገኘ 9	ልዩነት በትርፍ 10=9-8
1	የልጆች ቁምጣና ቲሸርት	-	ቻይና	በቁጥር	341	346	5++
2	የፍሪሲዮን ሪጄስ ፒንታ	-	ጃፓን	በቁጥር	1	7	6++
3	የመሪ ኮርቸር	-	-	በቁጥር	3	11	8++
4	የእግር ሽሚዝ	-	-	በቁጥር	0	12	12++
5	የእግር ቢሎን	-	-	በቁጥር	0	9	9++
6	ጎንራ	-	ቻይና	በቁጥር	1480	1891	11++
7	የአዋቂ ሽሚዝ	-	ቻይና	በቁጥር	910	916	6++
8	ብትን ሽት	-	ቻይና	በቁጥር	497	510	13++
9	አንሶላ	-	ቻይና	በቁጥር	288	297	9++
10	የልጆች ነጠላ ጫማ	-	ቻይና	በቁጥር	112	113	1++
11	ሻሽ	-	ቻይና	በቁጥር	1455	1474	21++
12	የሴቶች የውስጥ ልብስ	-	-	በቁጥር	91	92	1++
13	መቅለሚያ	-	ቻይና	በቁጥር	1641	1667	26++
14	የልጆች ጄኔስ ሱሪ	-	ቻይና	በቁጥር	50	51	11++
15							
16	የሴቶች የተዘጋጀ ቀሚስ	-	ቻይና	በቁጥር	17	19	2++
17	ሽርጥ	-	ቻይና	በቁጥር	122	123	1++
18	የዲሽ ጭቅላት	eurostar	ቻይና	በቁጥር	1261	1262	1++
19	ሽቶ	Bintalnur 50M/l	ቻይና	በቁጥር	111	113	2++
20	ሽጸ	AL-REHAD	-	በቁጥር	36	38	2++
21	የአይን መነፀር	-	-	በቁጥር	15888	15946	58++
22	DVD player	Miyota-DV480	ቻይና	በቁጥር	208	212	4++
23	Henna	MUMTAZ	ቻይና	በቁጥር	249	259	10++
24	Reciver	Eurostar-	ቻይና	በቁጥር	1	3	2++

25	ሺሻ	9200 አልፋክር	ቻይና	እስቲካ	286	289	3++
26	የጥፍር መቆረጫ	-	-	በፍሬ	12003	12004	1++
27	አሮጌ ልባሽ ጨርቅ	-	-	በኪሎ	255	266	11++
28	መድኀኒጽ	Vajga sung	-	በፓኬት	14533	14581	48++
29	ጥቃ ሽት	-	-	በቁጥር	350	352	2++
30	Satellite finder	-	-	በቁጥር	449	589	140++
31	የሸልቭ ቦክስ	-	ጃፓን	በቁጥር	50	55	5++
32	የመኪና ቸሪኪ	-	-	-	2	4	2++
33							
34	የልጆች ቀሚስና ሱሪ	-	-	በቁጥር	26	28	2++
35	Shim vzlve	13753-54260	japan	በቁጥር	34	35	1++
36	የእጅ ጓንት	-	-	በቁጥር	0	9	9++
37	Absorber shock	-	-	በቁጥር	0	1	1+

አባሪ 2

በሚሌ በቅ/ጽ/ቤት ያሉ ከ2002 ዓም በፊት ገብተው ርክክብ ያልተፈጸመባቸው /ውርስ ያልተደረጉ/ ተሽከርካሪዎች እና አጠቃላይ መረጃዎቻቸው

ተ.ቁጥር	ታርጋ ቁጥር	የተሽከርካሪ አይነት	ቻንሲ ቁጥር	መተር ቁጥር	ምርመራ
1.	280 D 36	TOYOTA (LANDCUIZER)	4164	HZ180-0003070	
2.	619 D 34	TOYOTA	4163	HDJ81-0000931	
3.	240 D 39	LAND CUIZER	የተገነጠለ	የተገነጠለ	
4.	513 D 37	SUZUKI VITRA	የማይነበብ	የማይነበብ	
5.	42 D 41 /(የኒላ ታታርጋ/	FEROZA DX	JDA00F30000039556	1589	
6.	168 D 36	NISSAN	የተቆለፈ		
7.	792 D 50	LAND CUIZER	የተቆለፈ		
8.	122 D 41	PATHFINDER	WDC1631541A064697	2663	
9.	915 D 47		የተቆለፈ		
10.	992 D 40		የተቆለፈ	የተቆለፈ	
11.	997 D 46	MERCEDEZ BENZ	የተቆለፈ	የተቆለፈ	
12.	489 D 48	MERCEDEZ BENZ	WDC1631541A064697	ሞተሩ አይከፈትም	
13.	379 D 32	LAND CUIZER	የማይነበብ		
14.	587 D 48	KIA	የተቆለፈ		
15.	870 D 48		የተቆለፈ		
16.	788 D 32	TOYOTA PIC UP	4164	HZ175LP- MR	

17.	109 D 47	TOYOTA DOUBLE CUP	2779	LN106L- PRMS
18.	312 D 48	HYUNDAI	በኮሪያኛ የተፃፈ	
19.	የእለት አአ1014	TOYOTA SINGLE CUP	የተቆለፈ	
20.	42 D 41	DAIHATSU	JDA00F30000064029	1589
21.	የሌለው	5-speed	የተቆለፈ	
22.	186 D 48			ሞተሩ አይከፈትም
23.	26392 (3 ኢ.ኢ.)	FUSO (MITSUBISHI)	520189	ሞተር ቁጥሩ የተፋቀ
24.	የእለት አአ1030	መለስተኛ የጭነት መኪና	የተቆለፈ	

በሚሌ ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት ከ2002 ዓ.ም. በፊት ጀምሮ ውርስ ሳይደረጉ የቆዩ ተሽከርካሪዎች በምን ምክንያት እንደገቡና የመኪኖች ባለቤት ማን እንደሆነና እስከ አሁን ባለ መኪኖቹ መጥተው ያልጠየቁበት ምክንያት ለመመዝገቢያ የተዘጋጀ ፎርም

ተ. ቁ.	የመኪና ባለቤት ስም	የመኪና ዓይነት	የመኪና ታ. ቁጥር	ጉምሩክ የገባበት ዓመት	የመኪናው ቁልፍ በማን እጅ ነው	ያቀረ ቡት ማስረ ጃ ብዛት	ጉምሩክ የገባበት ምክንያት	መኪናውን ለማውጣት እስከአሁን የቆየበት ምክንያት
01	አይድሩስ አብዱር ቃድር አሊ	ቶዩታ ባለ 1 ጋቢና	788D 32	2002 ዓ.ም	በእኔው በባለቤቱ	07	የጅቡቲ ታርጋ ስለነበረ ታርጋው ተቀይሮ በኢትጵያ ይሆናል ተብለን ነው፡፡	በግል ችግር ምክንያት
02	አብዱ አሊ መሀመድ	ቶዩታ ሃይሉክስ	870D 48	2002 ዓ.ም	በእኔው በባለቤቱ	10	የጅቡቲ ታርጋ ስለነበረ ታርጋው ተቀይሮ በኢትጵያ ይሆናል ተብለን ነው፡፡	ቀረጥ 520,000 ተጠይቀው በ3 ጊዜ ክፈሉ ተብለው ባለመቻላቸውና ቀረጡ ተቀንሶላቸው የክፍያ ጊዜውእንዲራዘምላቸው በተደጋጋሚ መጥተው ጠይቀው መልስ በማጣታቸው
03	ሁሴን አብዱ መሐመድ	ላንድክሩዘር	240 D39	2002 ዓ.ም	በእኔው በባለቤቱ	04	የጅቡቲ ታርጋ ስለነበረ ታርጋው ተቀይሮ በኢትጵያ ይሆናል ተብለን ነው፡፡	ቀረጥና ታክሱ በ2 አመት ተከፍሎ የሚያልቅ ይሆናል ተብለው ስልክ ቁጥር ሰጥተው ሄደው ነገር ግን ሳይደወልላቸው በመቅረቱ እና ባለንብረቱም መልሰው ለመምጣት የተለያዩ የግል ችግሮች ባለመምጣታቸው፡፡

04	አብዱ ሽኩር ሰድቅ	ኮብራ GXR 91	792 D 50	2002 ዓ.ም	በእኔው በባለቤቱ	06	የጅቡቲ ታርጋ ስለነበረ ታርጋው ተቀይሮ በኢትጵያ ይሆናል ተብለን ነው፡፡	ቀረጥና ታክሱ በጣም ስለበዛባቸው፡፡
05	ሰይድ አደም አቡበከር	ቶዩታ ጃጓር ባለ 1 ጋቢና	የዕለት 1014	2002 ዓ.ም	በእኔው በባለቤቱ	05	የጅቡቲ ታርጋ ስለነበረ ታርጋው ተቀይሮ በኢትጵያ ይሆናል ተብለን ነው፡፡	በግል ችር ምክንያት
06	ጎይቶም ገ/መድኅን	ሆንዳይ	312D48	2001 ዓ.ም	በእኔው በባለቤቱ	10	የጅቡቲ ታርጋ ስለነበረ ታርጋው ተቀይሮ በኢትጵያ ይሆናል ተብለን ነው፡፡	ቀረጥና ታክስ 420,000 ተጠይቀው አቅማቸው ስላልቻለ፡፡
07	ኡመር የሱፍ	ቶዩታ ሃይሉክስ	109Dd47	2001 ዓ.ም	በእኔው በባለቤቱ	04	የጅቡቲ ታርጋ ስለነበረ ታርጋው ተቀይሮ በኢትጵያ ይሆናል ተብለን ነው፡፡	ስልክ ይደወልላቸዋል ተብለው ባለመደወሉ እና በግል ችግር ምክንያት
08	ሙንትሃ ኢብራሂም ደብዮ	ሱዙኪ ፔትራ	186 D 48	2001ዓ.ም	በእኔው በባለቤቱ	04	የጅቡቲ ታርጋ ስለነበረ ታርጋው ተቀይሮ በኢትጵያ ይሆናል ተብለን ነው፡፡	ስልክ ይደወልላቸዋል ተብለው ባለመደወሉ እና በግል ችግር ምክንያት